# ፌደራሊዝም እና አንቀጽ 39

## ኢዛና ዘመንፈስ 07-30-17

ለመላው የሀገራችን ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እስከ መገንጠል የሚዘልቅ የራስን ጉዳይ በራስ የመወሰን ሕገ መንግስታዊ ሙብት ያጎናፀፋቸውን አንቀፅ 39ን ሲቃወሙ የሚደመጡ ወገኖች መኖራቸው የሚካድ ጉዳይ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን አንቀጽ 39 በዋነኛነት የሚያትተው፤ የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ካለፈው ታሪካችን የወረስናቸውን አሉታዊ የዕርስ በርስ ግንኙነቶች ደረጃ በደረጃ እያረሙ ሀገራዊ ወንድማማችነት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነትን መገንባት እንዲችሉ ለማድረግ ያለመ ግብ እንዳለው ቢሆንም፤ አብዛኞቹ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግን ለየራሳቸው ጠባብ ፍላጎት መሳካት በሚያመች መልኩ ሊተረጉሙት ሲሞክሩ ይስተዋላሉ፡፡ እናም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አንቀፅ 39 ላይ የተቃውሞ ጣታቸውን ሲቀስሩ ከምናውቃቸው ፖለቲከኞች ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው፤ የተቃውሚቸው አቀራረብ ቅኝት በሶስት የሚከፈል ይመስለኛል፡፡ እንዴት? የሚል ጥያቄ መነሳቱ ግድ ነውና እነሆ ለኔ እንደገባኝ አድርጌ ምላሽ ለመስጠት እሞክራለሁ፡፡

በዚህ መሰረትም የመጀመሪያዎቹ የሕገ መንግስታችንን አንቀፅ 39 አዘውትረው ሲቃወሙ የምናውቃቸው ወገኖች አቀራረብ፤ የቀድሞዎቹን አሀዳዊ ስርዓቶች አሁን ላይ ሀገራችን ከምትመራበት ፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር ይልቅ ለኢትዮጵያ የሚበጁ እንደነበሩ አድርገው የሚቆጥሩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የሁለተኛነቱን ደረጃ የሚይዝ ተቃውሞ ሲያቀርቡ የሚደመጡት ወገኖች ደግሞ፤ በተለይም እንደ ኢ.ነ.ግ ዓይነቶቹ ጠባብ ብሔርተኛ የፖለቲካ ቡድኖች የሚታወቁበትን የመገንጠል አጀንዳ የሚያራምዱ ወይም የሚደግፉና “አንቀፅ 39 ተግባራዊ ሊደረግ የማይችል ከሆነ ለምን አስፈለገ??” የሚል ቅሬታ አዘል ጥያቄ ከማንሳት የማይቦዝኑ ናቸው፡፡

ሶስተኛውን ረድፍ ሊወስድ የሚችል የአገም ጠቀም (ለዘብተኛ) ተቃውሞ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 39 ዙሪያ የሚያሰሙት ወገኖች ግን፤ ከሁለቱም የተቃውሞው ጎራ ፅንፈኝነት ከተጠናወታቸው የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት አስተሳሰብ አቀንቃኝ ቡድኖች፤ የተለየ ቅን ስጋት የሚሰማቸው እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ከዚህ የተነሳም “የአንቀፅ 39 ፎቢያ ያለባቸው ተቃዋሚዎች አሉ” የሚለው የአንዳንድ ታዛቢዎች አስተያየት በተለይም እነዚህኖቹን መሀል ሰፋሪ ወገኖች የሚመለከት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ይመስለኛል፡፡

ይህን የምልበት ዋነኛ ምክንያት ደግሞ፤ እነዚህኞቹ ወገኖች፤ ገዡው ፓርቲ ኢህአዴግ ለሚታወቅበት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፖለቲካዊ እሳቤ እጅጉን የቀረበ የሚመስል አመለካከት ያላቸው ሆነው ሳለ፤ ግን ደግሞ የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 39 ብቻ ለይተው ለመቃወም ሲሞክሩ የሚስተዋሉበት አግባብ በመኖሩ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፤ የአንቀፅ 39 መኖር አንዱ ብሔር፤ ወይም ብሔረሰብ ባሻው ቀን ብድግ ብሎ የመገንጠሉን አዋጅ እንዲያውጅ ሊጋብዝ ይችላል ከሚል ስጋታቸው በሚመነጭ ወላዋይ አቋምና ኢህአዴግን በመደገፍ መካከል ሲዋልሉ

የሚስተዋሉት ወገኖች፤ በእርግጥም "ፎቢያ" አሊያም ደግሞ ፍራቻ ያለባቸው እንጂ ለፖለቲካዊ ዓላማ ሲሉ ስርዓቱን እንደስርዓት የሚቃወሙ አይደሉም ማለት ይሆናል፡፡

በአንፃሩ የወደቀውን የአገዛዝ ስርዓት ከመናፈቅና ለመመለስ ከመሻት የሚመነጭ ትምክህተኛ አቋም በማራመድ የሚታወቁትም ሆኑ ከነርሱ በተቃራኒ የሚፈረጀውን የጠባብ ብሔርተኝነት አስተሳሰብ የሙጥኝ ያሉት የፖለቲካ ቡድኖች፤ ስርዓቱ ላይ የሚያሳዩት ተቃውሞ፤ መሰረታዊ ሊባል ለሚችል የራሳቸው ድብቅ አጀንዳ ማሳኪያነት የሚደረግ ጥረት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህም ይመስላል የሁለቱን ተቃራኒ ፅንፎች ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ወክለው የሚንቀሳቀሱት የተቃውሞው ጎራ ቡድኖች፤ አንቀፅ 39ኝን የሚያወግዙበት አግባብ የተለያየ ቅኝትን የተከተለ ሲሆን የሚስተዋለው፡፡ ለአብነት ያህልም፤ በቀደሙት ስርዓተ መንግስታት ዘመን፤ የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ከአሁኑ በተሻለ ሀገራዊ የአንድነት መንፈስ ዕርስ በርሳቸው ተፈቃቅደው ይኖሩ እንደነበር አድርገው የሚወስዱት ወገኖች፤ ስለዚያን ጊዜው የብሔር ጭቆና የሚነሳውን ሃሳብ ሁሉ "ወያኔ ኢህአዴግ ከፋፍሎ ለመግዛት እንደያመቸው ሲል የፈጠረው ተረት ተረት እንጂ እውነት አይደለም" የሚል ማስተባበያ ከመስጠት ቦዝነው እንደማያውቁ ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

በነኦ.ነ.ግ ፊታውራሪነት "እንታገልለታለን" የሚሉትን የአንድ ብሔር ወይም ብሔረሰብ ህዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ነጥለው ለመግዛት ያለመ የተቃውሞ ፖለቲካን ለማሳካት "በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ" የሚገለፅ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የሚስተዋሉት ጠባብ ብሔርተኛ ቡድኖች አንቀፅ 39 ላይ የሚያሰሙት ቅሬታ ግን "እኛ እንደምንፈልገው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መገንጠል እንድንችል ካልተፈቀደልንማ የአንቀጹ መኖር እንዲያው ዝም ብሎ ለይስሙላ ያህል ብቻ ሕገ-መንግስቱ ውስጥ እንደተካተተ ይቆጠራል" የሚል ነው እንጂ የሕጉን አስፈላጊነት የመቃወም አዝማሚያ አያሳዩም፡፡ ምክንያቱም ደግሞ ትምክህተኝነት የተጠናወተውን የግዛት አንድነት ናፋቂ አስተሳሰብ ወክለው የፌደራሊዝም ስርዓቱን በመቃወም የሚታወቁት ፅንፈኛ የፖለቲካ ኃይሎች የቀደሙት አሃዳዊ ስርዓቶች ይከተሉት ከነበረው አድሏዊ ፖሊሲ የሚመነጭ ፈርጀ ብዙ ጭቆና በመላው የሀገራችን ብሔር ብሔረሰቦች ላይ ሲፈፀምባቸው ስለመቆየቱ የሚወሳውን ታሪካዊ እውነታ "ወያኔ ኢህአዴግ ሆነ ብሎ የፈጠረው ተረት ተረት" እንደሆነ አድርገው የሚወስዱትን ያህል፤ በነኦ.ነ.ግ መሪ ተዋናይነት የሚንቀሳቀሱት ጠባብ ብሔርተኛ ቡድኖች ደግሞ "አሁንም ድረስ የአቢሲንያ ኤምፓየር ገዥ መደቦች ከሚፈፅሙብን ብሔራዊ ጭቆና ገና አልተላቀቅንም" ሲሉ የሚደመጡበት አግባብ አለና ነው፡፡

ኦ.ነ.ግና መሰሎቹ ለዚህ ቅሬታቸው እንደብቸኛ የመፍትሔ አቅጣጫ የሚያስቀምጡትም "ስትፈልግ እቺ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በአፍጢሟ ትደፋ እንጂ እኛ ኦሮሚያን ገንጥለን የራሳችንን ነፃ መንግስት መመስረታችን አይቀርም" የሚል እንደሆነም ተነግሮ ያበቃ ጉዳይ ነው፡፡ እንግዲያውስ የዛሬዋ ኢትዮጵያ የምትመራበትን ፌዴራላዊ፤ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግስት በፀረ የሀገር አንድነት ፈርጀው የወደቀውን አሀዳዊ ስርዓት ለመመለስ ያለመ ተቃውሞ

ሲያካሒዱ በምናውቃቸው የትምህክት ሃይሎች ፖለቲካዊ እሳቤና እንዲሁም የራሳቸውን የብሔር ብሔረሰብ ህዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ነጥለው ለመግዛት በሚሹት ጠባብ ብሔርተኛ ቡድኖች ፅንፈኛ አመለካከት መካከል፤ ፈፅሞ ሊታረቅ የማይችል መሰረታዊ የአቋም ልዩነት አለ የምንለውም ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ይልቅስ ከላይ ለአብነት ያህል እንደተጠቆመው ሁሉ፤ ካለፈው የጋራ ታሪካችን የወረስናቸውንና በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ተፈፅመው አሉታዊ ውጤት ያስከተሉትን የመንግስታት ስህተቶች፤ ዳግመኛ እንደማይከሰቱ የሚያረጋግጥ ሕገ-መንግስታዊ የእርምት እርምጃ የመውሰድን አስፈላጊነት ከመረዳት በመነጨ ሀገራዊ መግባባት ተቃኝቶ፤ ለዘለቄታዊ የህዝቦቻችን ጤናማ የዕርስ በርስ ግንኙነት መዳበርና ከመሰጋጋት የፀዳ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ለመፍጠርም ጭምር ሲባል አስፈላጊነቱ የታመነበትን የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 39፤ ሁለቱ የተቃውሞው ጎራ ፖለቲካ መሪ ተዋኒያን ፅንፈኛ ቡድኖች የሚያዩበት መነፅር እንደ ምድር ዋልታ እጅጉን የተራራቀ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት እንጂ፡፡

ምንም እንኳን ትምክህትና ጠባብ ብሔርተኝነት ተብለው የሚፈረጁትን ሁለት ዓይነት የፖለቲካዊ አስተሳሰብ ጽንፎች ወክለው በሚንቀሳቀሱት የተቃውሞው ጎራ ኃይሎች መካከል የሚሰተዋለው መሰረታዊ የአቋም ልዩነት የዚህን ያህል ጎልቶ የሚንጸባረቅ ጥሬ ሀቅ የመሆኑ ጉዳይ ባያከራክርም፤ አሁን አሁን ከወደ ባህር ማዶ የሚደመጡ የቡድኖቹ ካድሬዎች ግን “ወያኔ ኢህአዴግ ሆነ ብሎ አማራንና ኦሮሞን ለማጣላት ሲል የሚያናፍሰው ፕሮፓጋንዳ ነው እንጂ እኛ አንድ ነን” እንደማለት የሚቃጣውን ማምታታት ፈሊጥ አድርገውታል፡፡ ይልቁንም ደግሞ የሁለቱን ጽንፎች ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ወክለው የፌደራል ስርዓቱን በሃይል ለማስወገድ ያለመ የትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ ስለመሆናቸው ተደጋግሞ የተነገረላቸውን የሽብር ቡድኖች በማውገዝ ፋንታ የሚያበረታቱ አንዳንድ ታዋቂ የሀገራችን ምሁራን እያበረከቱ ያለው አሉታዊ አስተዋጽኦ አሳሳቢም፤ አስተዛዛቢም ሆኖ ይሰተዋላል፡፡

ከዚህ አኳያ እንደ አብነት መነሳት የሚገባው ጉዳይ መስሎ የሚሰማኝም ደግሞ፤ በተለይ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ የተባሉ ዲያስፖራ ምሁር “የኦሮሞና የአማራ ትክክለኛ የዘር አመጣጥ” በሚል ርዕስ ጽፈውት ልክ የዛሬ ዓመት ገደማ ከታተመው ታሪክ ቀመስ መጽሐፍ ጋር በተያያዘ መልኩ ሲውጠነጠን የታዘብነው አስነዋሪ ፖለቲካዊ ሴራ ነው፡፡ ይህን የምልበት ዋነኛ ምክንያትም፤ ግለሰቡ ተጠቃሹን መጽሐፋቸውን በዚያ መልኩ አዘጋጅተው እንዲያሳትሙ የተደረገበት አግባብ፤ የፌደራል ስርዓቱን በፀረ የሀገር አንድነት ፈርጀው፤ የስርነቀል ለውጥ ጉዞውን ለመቀልበስ ያለመ የአመጽ ተግባር ለመቀስቀስ ከመሞከር ቦዝነው የማያውቁት የትምክህት ጎራ ታቃዋሚ ፖለቲከኞች የሰጧቸውን ድርጅታዊ ተልእኮ ለመወጣት ሲሉ እንጂ የኦሮሞንና የአማራን ህዝቦች ለማቀራረብ እንዳልሆነ መረዳት አያዳግትምና ነው፡፡ እኚሁ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶለሳ ጅግሳ የተባሉ ዲያስፖራ ምሁር “የኦሮሞና የአማራ ትክክለኛ የዘር አመጣጥ” የሚል ርዕስ ስላለው አዲስ መፀሐፋቸው ባለፈው መስከረም ወር 2009 ዓ.ም ለሰንደቅ ጋዜጣ የሰጡትን ቃለ ምልልስ ያነበብን ሰዎች እንደምናስታውሰውም “ትምክህትና ጠባብ ብሔርተኝነት የሚባል አስተሳሰብ የለም፤ ሊኖርም አይችልም” ሲሉ አስረግጠው ነግረውናል፡፡ ስለሁለቱ የአመለካከት ችግሮች የሚነሳው ነገር ሁሉ በተለይም

ትግርኛ ተናጋሪ የገዥው ፓርቲ ፖለቲከኞች “ለከፋፍለህ ግዛ ስትራቴጂያቸው ማስፈፀሚያነት የፈጠሩት ተረት ተረት እንጂ በእውን መሬት ላይ የሚስተዋል ጉዳይ እንዳልሆነም” ነው ግለሰቡ በገደምዳሜ የገለፁልን፡፡

ፕሮፌሰሩ በዚያው የሰንደቅ ጋዜጣ ቃለ ምልልሳቸው ላይ “በነገስታቱ ዘመነ መንግስት ህዝቡ ከየሚኖርበት የገጠር አካባቢ ወደ ቤተ መንግስት እየመጣ ሊፈታልኝ ይገባል የሚለውን ማንኛውንም ዓይነት ችግር ለራሳቸው ለንጉሰ ነገስቱ የሚያቀርብበት አሰራር ስለነበር የዚህን ያህል ለአመፅ የሚጋብዝ ብሶት አይተን አናውቅም” ሲሉ የሰጡት አስገራሚ አስተያየት ደግሞ ብሔራዊ ጭቆና ይፈፀም ነበር ሲሏችሁ እንዳታምኑ ተረት ተረት ነው የሚል አንድምታ ያዘለ ሆኖ ነው የተሰማኝ ለእኔ፡፡

ለማንኛውም ግን ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጅግሳን አንስቼ እቺን ያህል ስለርሳቸው አሉታዊ ሚና ማውሳቴ፤ ግልሰቡ በደምና በአጥንት የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ስለመሆናቸው ቢነገርላቸውም፤ የአስተሳሰብ ወገንተኝነታቸው ግን፤ የአንቀጽ 39 “ፎቢያ” ሰለባዎች ተደርገው ከሚወሰዱት ትምክህተኛ የተቃውሞው ጎራ ፖለቲካ ልሂቃን ተርታ የሚያስመድባቸው ሆኖ ስለተሰማኝም ጭምር ነው፡፡ በተረፈ እኔ እንደ አንድ የዚህች አገር ዜጋ፤ የህገመንግስታችን አንቀጽ 39 የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ካለፈው የጋራ ታሪካችን የተወረሱ እርስ በርስ የመሰጋጋት ጥርጣሬዎችን አስወግደው፤ በምትኩ አንድ ሌላውን የጎሪጥ እያየ የሚኖርበት ምንም ምክንያት እንደሌለ የሚያረጋግጥ የመተማመን ስሜት በመካከላቸው ለማስፈን ይችሉ ዘንድ የተቀመጠ የመፈቃቀድ ዋስትና እንጂ ለብተናም፤ ለጭቆናም የሚጋብዝ ሆኖ አይሰማኝም፡፡ ስለዚህም (ዝኒከማሁ) አንቀጽ 39 ላይ የተቃውሞ ጣታቸውን በመቀሰር የሚታወቁት ወገኖች፤ ከተጠናወታቸው አጉል ፍራቻ የመላቀቅ ፍላጎት ካላቸው ህገ መንግስታዊ እሳቤውን ከጭፍን ስሜታዊነት በጸዳ መንፈስ ማጤን ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ ለማንኛውም እኔ እዚህ ላይ አብቅቻለሁ፡፡